# የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ቦንድ ቶምቦላ ሎተሪ

ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ገቢ ለማሰባሰብ የግድቡ ግንባታ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት የተለያዩ መርሃ ግብሮችን ቀርጾ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ከነዚህ የገቢ ማሰባሰብያ መርሃ ግብሮች አንደኛው የቶምቦላ ሎተሪ ሲሆን በአገር ውስጥ ተግባራዊ ተደርጎ ትልቅ ውጤት አስገኝቷል። በሎተሪው ከተካተቱት ዕጣዎች የመኖሪያ ቤትና ተሽከርካሪዎች ዋነኞቹ ሲሆኑ ሌሎች በርካታ አጓጊ ዕጣዎችንም አካቷል።

በመርሃ ግብሩ በመላው ዓለም የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያንም እንዲሳተፉበት የሎተሪው ትኬት በሁሉም የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንስላ ጽ/ቤቶች እየተሸጠ ይገኛል። የአንድ የሎተሪ ትኬት ዋጋ አስር (10) የአሜሪካ ዶላር ሲሆን በዕጣው ከተካተቱት ትልቅ ዋጋ ያላቸው የመኖሪያ ቤትና ተሽከርካሪዎች ይገኙበታል። በመሆኑም በኖርዲክ አገራት የምትገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን በመርሃ ግብሩ በመሳተፍ የሁሉም ኢትዮጵያውያን አሻራ ላረበት ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ያላችሁን ወገንተኝነት እንድታሳዩ እንዲሁም የዕጣዎቹ ተቋዳሽ እንድትሆኑ ጥርአችንን እናቀርባለን።

መልካም እድል!!